የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 17
ADDIS ABABA 17th February 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፫/፪ሺ፮ ዓ.ም

ለሁለተኛው አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...ገጽ ፯ሺ፪፻፵፱

CONTENTS

**Proclamation No. 823/2014**

**International Development Association Financing Agreement for Financing the Second General Education Quality Improvement Project II, Ratification Proclamation .................. Page 7249**

**አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፫/፪ሺ፮**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሁለተኛው አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፹፭ ሚሊዮን ፰፻ሺ. ኤስ.ዲ..አር (ሰማኒያ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺ. ኤስ.ዲ..አር.) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ.፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳ ቀን ፪ሺ.፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No. 823/2014.**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount equivalent to 85,800,000 SDR (eighty five million eight hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Second General Education Quality Improvement Project, was signed in Addis Ababa on the 5th day of December, 2013.

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 28th day of January, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው አጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፫/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፭ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 5315-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፭ ሚሊዮን ፰፻ሺ. ኤስ.ዲ.አር (ሰማኒያ አምስት ሚሊዮን ስምንት መ ቶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Financing the Second General Education Quality Improvement Project II, Ratification Proclamation No. 823/2014".

**2. Ratification of the Agreement**

The Financing Agreement Credit number 5315-ET signed on December 5th 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of equivalent to 85,800,000 SDR (eighty five million eight hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of February, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**